# ከራስ በላይ ነፋስ!

ሶቅራጥስ



Σωκράτης

“ራስን ካላወቁ ከንቱ ነው ማወቅ!”
ብሎ የጨረሰው ያ ታላቁ ሊቅ
የዓለም ፈላስፋ አወይ ሶቅራጥስ
እጅጉን ይልቃል ከራስጣጣልስ!

ራስን መጣል እስቲ አረ ለምን ነው?
የራሱን ማንነት በውል ሳያወቀው
የዓለምን ጥበብ ቢመራመር ሰው
ከንቱ መቅረት እንጂ የታለ ፋይዳው?

ወደ ባሕላችን፣ ወደ ታሪካችን
ቶሎ ካልተመለስን በገዛ ራሳችን
ከቶ አይቀሬ ነው ከንቱ መጥፋታችን!
“ከራስ በላይ ነፋስ!” ብሏል ወገናችን።

ገ/ኢ. ጐርፉ።

አራስጣጣልስ



Ἀριστοτέλης